| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ፡፡ |
| ርእስ ፤ | "ሕዝብ ፡ ይንገሥ ፤ ሥልጣኔ ፡ ይመለስ ፡፡ " |
| ደራሲ ፤ | ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ጽ. ፡ ቤት ፡፡ |
| ዕለት ፤ | ሚያዝያ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡፡ |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ፡፡ |
| መጽሔት ፤ | ሥልጡንሕዝብና ፥ ቍ.2011.001 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ፡፡

## editorial | éditorial

## *"ሕዝብ ፡ ይንገሥ ፤ ሥልጣኔ ፡ ይመለስ ፡፡ "*

ጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ በነሲብ ፡ አልተገኘችም ፥ በሥልጣኔ ፡ እንጂ!

ዘንድሮ ፡ የዕረፍታቸውን ፡ 10 ኛ ፡ ዓመት ፡ የምናስታውሰው ፥ የኢትዮጵያ ፡ የቍርጥ ፡ ቀን ፡ ልጅ ፥ ሊ.ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሥልጣኔ ፦ *"ሥልጡንሕዝብና"* ፡ ብለው ፥ ቃልን ፡ ከምስጢር ፡ አስማምተውና ፡ አዋዶው ፥ በሀገርኛ ፡ ሰምየውልናል ፤ ወዶን ፣ ፈቅደን ፡ ተቀብለነዋል ፡፡ አዎን! ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጥንታዊት ፡ ሥልጣኔ ፡ ናት ፡፡ ከጥንት ፡ ከመሠረት ፡ በርትዕ ፣ በሕግና ፡ በሥርዐት ፡ የተመራች ፡ ሀገር ፤ ሕዝቧም ፡ ገዢዎቹን ፡ ሲሾም ፡ ሲሽር ፡ የኖረ ፡ ሥልጡን ፡ ሕዝብ ፤ ዐዳሩም ፡ የሥልጡንሕዝብና ፡ ዐዳር ፡ ነው ፡፡ ይህም ፡ በመኾኑ ፥ ኢትዮጵያና ፡ ሕዝቧ ፥ የመጣባቸውን ፡ ፀረ–ሥልጣኔ ፡ አጥቂ ፡ ኀይል ፡ ኹሉ ፥ በሥልጣኔ ፡ ያጠሉበትን ፡ ያኽል ፡ በጦርም ፡ ደምስሰው ፡ እየመለሱት ፥ ለሺ ፡ ዓመታት ፡ በሐራ ፡ ሀገርነትና ፡ በሐራ ፡ ሕዝብነት ፡ ኖረው ፡ እዘመናችን ፡ ደርሰዋል ፡፡

የዘመናችንም ፡ *"ዴሞክራሲ"* ፥ ውስጠ ፡ ምስጢሩ ፡ ሲመረመር ፥ ያው ፡ *"ሥልጡንሕዝብና"* ፡ ነው ፡፡ ሥልጡንሕዝብና ፡ ግን ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ነው ፡፡ የ*"ዴሞክራሲ"* ፡ ዐይነተኛው ፡ መገለጫው ፡ *"አንድ ፡ ሰው ፥ አንድ ፡ ድምፅ"* ፡ የሚለው ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ የኾነውን ፡ ያኽል ፥ ሥልጡንሕዝብና ፡ ደግሞ ፡ በውስጡ ፡ ሥልጡንነትን ፡ (ማለት ፥ በፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ የርትዕ ፡ አክብሮትን) ፡ ከጠባዩ ፡ ጋራ ፡ አዋሕዶ ፥ ለ*"ፋሺዝምና"* ፡ እና ፡ ለመሳሰለው ፡ የስግብግብነትና ፡ የራስ ፡ ወዳድነት ፡ ዝንባሌዎች ፡ በምርጫም ፡ እንኳ ፡ መግቢያ ፡ ቀዳዳን ፡ ይነሣል ፤ ሀገርንና ፡ ሕዝብን ፡ ይጠብቃል ፤ ለአህጉራዊ ፡ ሰላምም ፡ ዘብ ፡ ይቆማል ፡፡ የኢትዮጵያ ፡ የህልውና ፡ ዋስትና ፡ ሌላ ፡ ምስጢር ፡ የለውም ፤ ይኸው ፡ ሥልጡንሕዝብናዋ ፡ ነው ፡፡

በኋላኛው ፡ ምእትያ ፥ ኢትዮጵያን ፡ ታላቅ ፡ ስብራት ፡ አግኝቷታል ፡፡ ስብራቱ ፥ የንጉልዮሽ ፡ (የ*"ኒኒሊዝም"*) ፡ ስብከትና ፡ አደራረግ ፡ ያስከተለው ፡ የሥርዐት ፡ መጠንጠን ፡ ውጤት ፡ ኾኖ ፥ እንሆ ፥ ዛሬ ፡ ሀገሪቱ ፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ባዕድ ፡ ተከል ፡ የአፓርትሀይድ ፡ ሥርዐት ፡ እንድትበታተን ፡ ኾና ፥ በማያቋርጥ ፡ የ*"ዘር ፡ ማጽዳት"* ፡ ፍጅትና ፡ ከርከሬሻ ፡ ትተራምሳለች ፡፡ ችግራችን ፡ እንዴትና ፡ በማን ፡ ይፈታ ፧ ዐዲሱስ ፡ ሥርዐት ፡ እንዴትና ፡ በማን ፡ ይሠራ ፧ የሚሉት ፡ ጥያቄዎች ፡ የእያንዳንዳችን ፡ ሀገራውያንን ፡ ኅሊና ፡ ዘልቀው ፥ የሥራ ፡ ድቅናችን ፡ ኾነዋል ፡፡

ሀገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ የእኛ ፡ የሀገራውያኑ ፡ እናታችን ፣ ቤታችን ፤ ከእኛም ፡ ዐልፎ ፥ የባዕዳን ፡ መትረፊያቸው ፣ መጠጊያቸው ፡ ናት ፡፡ *"የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ – ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ."* ፥ የተደቀነብንን ፡ የሀገራዊ ፡ ህልውና ፡ አደጋ ፡ ለመቋቋም ፡ ከ 1967 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ ይታገላል ፡፡

ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ በተመሠረተበት ፡ በሥልጡንሕዝብና ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችንን ፡ ዳግመኛ ፡ አደራጅተንበት ፥ ሕዝባዊ ፡ እግዚእናችንን ፡ የማስከበርና ፡ ሀገራችንን ፡ የመዋጀት ፡ የተቀደሰ ፡ ዐላማን ፡ እዳር ፡ እንድናደርስ ፡ ጥሪውን ፡ ለመላ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ያስተላልፋል ፡፡ አቤት! ፡ ልንለው ፡ ሀገራዊነታችን ፡ ያስገድደናል ፡፡ አዎን! ፡ ዛሬ ፥ ራስ ፡ ወዳድነት ፡ በሀገሪቱ ፡ ሰፍኖ ፥ ጥቂቶች ፡ በጐጥ ፡ በቀዬ ፡ ተቧድነው ፥ *"እኔ ፡ ነኝ ፡ የምነግሠው! ፡ ... ፡ የለም ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ የምነግሠው!"* ፡ በሚባባሉበት ፡ ሰዓት ፥ ባንድ ፡ ድምፅ ፦ *"ሕዝብ ፡ ይንገሥ ፤ ሥልጣኔ ፡ ይመለስ ፡፡ "* ፡ ልንላቸውና ፡ ልናሳምናቸው ፥ ከዚህም ፡ በላይ ፥ እግዚእናችንን ፡ አስከብረን ፥ ዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ ሠርተን ፥ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ ልናቋቁም ፡ ይገባል ፨


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡፡